የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፫
አዲስ አበባ መስከረም ፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.83
ADDIS ABABA,19th September 2017

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻፲፩/ ፪ሺ፱ ዓ.ም
የብሔራዊ ደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ................ገፅ ፱ሺ፰፻፺፩

**CONTENT**

Council of Ministers Regulation No. 411/2017
National Bio-safety Advisory Committee Establishment Council of Ministers Regulation …………………....Page 9891

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲፩/፪ሺ፱**

**የብሔራዊ ደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀፅ ፭ እና የደህንነተ ሕይወት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፭/፪ሺ፩ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፺፮/፪ሺ፯ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፪ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡

**Council of Ministers Regulation No. 411/2017**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF NATIONAL BIO-SAFETY ADVISORY COMMITTEE**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 22 of the Bio-safety Proclamation No. 655/2009 (as amended by Proclamation No. 896/2015).

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የብሔራዊ ደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲፩/ ፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PART ONE
## GENERAL

### 1 .Short Title

This Regulation shall be cited as the "National Bio-safety Advisory Committee Establishment Council of Ministers Regulation No. 411/2017".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩/"ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

፪/"አዋጅ" ማለት የደህንነተ ሕይወት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፭/፪ሺ፩ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፺፮/፪ሺ፯ እንደተሻሻለ) ነው፤

፫/በወንድ ፆታ የተገለፀው ድንጋጌ ሴትንም ያካትታል።

## ክፍል ሁለት
## የብሔራዊ ደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ

**፫. መቋቋም**

፩/የብሔራዊ ደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ በዚህ ደንብ ውስጥ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/የኮሚቴው ተጠሪነት ለሚኒስትሩ ይሆናል።

**፬. ዓላማ**

የኮሚቴው ዓላማ ደህንነተ ህይወትን በሚመለከት መንግስትን ማማከር ነው።

**፭. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት**

ኮሚቴው፡-

፩/በልውጠ ህያዋን እንቅስቃሴ፣

፪/በደህንነተ ህይወት ጉዳዮች የሚወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች፣

፫/በልውጠ ህያዋን እንቅስቃሴ በተመለከተ ለማህበረሰብ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያግዙ ውጤታማ ዘዴዎች መለየት እና

፬/በማናቸውም የደህንነተ ህይወት ጉዳዮች ላይ ከሚኒስትሩ በሚቀርብ ጥያቄ ወይም ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በሚኒስትሩ በኩል በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት መንግስትን የማማከር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

**2. Definition**

In this Regulation:

1/"Ministry" and "Minister" means the Ministry and Minister of Environment, Forest and Climate Change, respectively;

2/"Proclamation" means the Bio-safety Proclamation No. 655/2009 (as amended by Proclamation No. 896/2015);

3/any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO
## NATIONAL BIOSAFETY ADVISORY COMMITTEE

**3. Establishment**

1/ The National Bio-safety Advisory Committee (in this Regulation to be referred as the "Committee") is hereby established.

2/ The committee shall be accountable to the Minister.

**4. Objective**

The objective of the Committee shall be to advise the Government on issues related to bio-safety.

**5. Powers and Duties of the Committee**

The Committee shall, upon request by the Minister, or by the request of other ministries through the Minister have the powers and duties to advise the Government on:

1/transactions of genetically modified organisms;

2/the issues of national policies and laws of bio-safety;

3/identifying effective methods to create public awareness regarding transactions of genetically modified organisms;

4/ on any other matters related to bio-safety

www.chilot.me

**፮. <u>የኮሚቴ አባላት</u>**

፩/የኮሚቴው አባላት ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ጨምሮ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

፪/የኮሚቴው አባላት አግባብነት ያለው ሙያዊ ክህሎትና ልምድን እንዲሁም ተቋማዊ አግባብነት ያለው ውክልናን መሠረት በማድረግ ከመንግሥታዊ አካላት እንዲሁም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ብዙሃን ማህበራትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት የተውጣጡ ይሆናል።

፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚቋቋመው ኮሚቴ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ የሚከተሉትን የሙያ ስብጥሮች የሚያካትት ይሆናል፦

ሀ)ባዮቴክኖሎጂ፤

ለ)በዘረመል ምህንድስና፣

ሐ)የብዝሃ ህይወት፣

መ)የተፈጥሮ ሳይንስ፣

ሠ)የአካባቢ ሳይንስ፣

ረ)የህክምና ወይም የጤና ሳይንስ

ሰ)የምግብ ሳይንስ

ሸ)የእንስሳት ሳይንስ

ቀ)በማኅበራዊ ሳይንስ እና

በ)እንደ አስፈላጊነቱ አግባብ ያለውን ሌላ ሙያ ዘርፍ።

**፯. <u>የኮሚቴው ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>**

የኮሚቴው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ ኮሚቴውን ይሰበስባል፣ ሥራዎች ይመራል፤

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን ኃላፊነትና ተግባራት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፫/ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል።

**6. <u>Members of the Committee</u>**

1/The Committee members, including the Chairperson and Deputy Chairperson, shall be nomination by the Minister and be assigned by the Government; and their numbers shall be determined as appropriate

2/The Committee shall be comprised of members with relevant qualification, experience and organizational representations from government bodies, higher education institutions, civil societies and non-governmental institutions.

3/Without prejudice to sub-article (2) of this Article the Committee shall be drawn from different institutions comprise the following professional:

a)Biotechnology;

b)Genetic Engineering;

c)Biodiversity;

d)Natural Science;

e)Environmental Science;

f)Medical or Health science;

g)Nutrition Science;

h)Animal Science;

i)Social Science and

j)other disciplines as appropriate.

**7. <u>Powers and Duties of the Chairperson</u>**

The Chairperson of the Committee shall have the following powers and duties:

1/preside and lead the activities of the committee;

2/cause the execution of powers and duties defined in Article 5 of this Regulation;

3/call regular and extraordinary meetings.

www.chilot.me

**፰. ስለኮሚቴው ስብሰባ**

፩/ ኮሚቴው ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ በሰብሳቢው ጥሪ ኮሚቴው በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል።

፫/ ከኮሚቴው አባላት ከሁለት ሦስተኛው በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡

፬/ የኮሚቴው ምክረ ሀሳብ በስምምነት የሚተላለፍ ይሆናል፤ ልዩነት በሚፈጠር ወቅት አብላጫው ምክረ ሀሳብ እና የልዩነት ሀሳቦች ተካተው ለሚኒስትሩ ይቀርባሉ።

**፱. የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን**

፩/የኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለሶስት ዓመት ይሆናል።

፪/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስትሩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር የኮሚቴ አባል በድጋሚ ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን እንዲሰየም ማድረግ ይችላል።

**፲. ምስጢር ስለመጠበቅ**

፩/በኮሚቴው በይፋ እንዳይወጣ የተወሰነን መረጃ የኮሚቴው አባላት ሚስጢራዊነቱን መጠበቅ አለባቸው።

፪/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን የተላለፈ የኮሚቴ አባል አግባብነት ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

**ክፍል ሶስት**

**የብሔራዊ ደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት**

**፲፩. ጽሕፈት ቤት**

የብሔራዊ ደህንነተ ሕይወት አማካሪ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት በሚኒስቴሩ ስር የሚደራጅ ይሆናል።

**፲፪. የጽሕፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት**

ጽሕፈት ቤቱ ፡-

፩/ማንኛውንም የደህንነተ ህይወት ጥያቄ በማደራጀት ለኮሚቴው ያቀርባል፤

፪/የኮሚቴውን ምክረ ሀሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

፫/የኮሚቴውን የክንውን ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚኒሰትሩ ያቀርባል፤

**8. Meetings of the Committee**

1/The Committee shall hold its regular meeting at least four times a year.

2/Without prejudice to sub-article (1) of this Article the committee may have extraordinary meeting any time upon the call of the Chairperson.

3/There shall be a quorum where more than two third of the members of the Committee are present at a meeting.

4/The Committee shall present its recommendation in consensus provided, however, if consensus is not reached, the majority recommendation together with the dissenting opinion shall be sent to the Minister.

**9. Terms Committee members**

1/The term of office of the Committee members shall be three years.

2/Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the Minister may, in consultation with appropriate body, assign a member of committee for one additional term.

**10. Confidentiality**

1/The Committee members shall keep any information that has been decided not to be disclosed.

2/Any Committee member who violates sub-article (1) of this provision shall be liable according to relevant laws.

**PART THREE**

**NATIONAL BIOSAFETY ADVISORY COMMITTEE SECRETARTIAT**

**11 .Secretariat**

The Secretariat of the National Bio-safety Advisorv Committee shall be organized under the Ministry.

**12 .Powers and Duties of the Secretariat**

The Secretariat shall:

1/organize and submit any bio-safety requests made to the committee;

2/submit the recommendation of the Committee to the Minister;

3/prepare and submit performance report of the Committee to the Minister.

www.chilot.me

፬/የኮሚቴውን ምክረ ሀሳብ እና ሌሎች ሰነዶችን በአግባቡ አደራጅቶ ይይዛል።

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፲፫. መመሪያ ስለማውጣት**

ይህን ደንብ ለማስፈጸም ሚኒስቴሩ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፲፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም ፱ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ኃይለማሪያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

4/compile and maintain recommendations and other documents of the Committee.

**PART FOUR**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**13.Power to Issue Directive**

The Minister may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

**14.Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa this 19th day of September , 2017**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me